የኢትዮጵያውያን ሕዝባዊ ማህበራት ጉባኤ (ኢሕማጉ)
Congress of Ethiopian Civic Associations (CECA

# የኢ.ሕ.ማ.ጉ. መግለጫ

## <u>የሃኪሞች ጥያቄዎች ወቅታዊና ፍትኃዊ ስለሆኑ ልንደግፋቸው ይገባል!!</u>

ሜይ 22፣ 2025 ዓ.ም

ሕገ-መንግስታዊ ስርዓት በሰፈነባቸው አገራት ሉዓላዊ ዜጎች ብሶታቸውን ለመንግስት በተናጠልም ሆነ በሙያ ማህበር ስም የማቅረብ ብቻ ሳይሆን አስቸኳይ መፍትኄ የማግኘት መብታቸው የተከበረ ነው። በመንግስት የጤና ተቋማት የሚሰሩ ዶክተሮችና የጤና ባለሙያዎች የደመዎዝና የተያያዙ አገልግሎቶች መስተካከል አንገብጋቢነትን ባለፉት አመታት ሲወተውቱ ቆይተዋላ።

ኢትዮጵያን የማይመጥነው እብሪተኛና ሙሰኛ የብልጽግና አስተዳደር ግን ጆሮ ዳባ ብሎ፤ በጀቱን ከትምህርትና ከጤና አገልግሎቶች በማሸጋሸግ የርስ-በርስ ጦርነቶችንና የቅንጦሽ ሕንጻዎችና የከተማ ብልጭልጭ መንገዶችን ሲሰራባቸው ከርሟል። ይባስ ብሎ በሰላማዊ የቀረቡለትን የዳቦ ጥያቄዎች በማጥላላት፣ መሪዎችን በማስፈራራትና ብሎም እስርቤት በማጎር፣ ብዙሃኑ የስራ ማቆም አድማ እንዲወስዱ አስገድዷቸዋል። ጦርነትን እንዳሸን በማፍላት እድሜውን ሊያራዝም የሚጥረውና መደራደር ፍጹም የማይሻው ብልጽግና "አድማ በታኝ" ሃኪሞችን ለመመልመል የስራ ማስታዎቂያዎች ማውጣም ጀምሯል። ነገሮች ከድጡ ወድማጡ እየመጡ ጥያቄው ከደመዎዝ ጭማሬ አልፎ ወደ የሃገር ህልውናን የማዳን ርብርቦሽ ተሻግሯል።

ከዚህ በፊት በኃይማኖት ተቋማት፣ በቅርቡም በአማራ የሕልውና ትግል እንደታየው የችግሩ መሰረት ስር ሰደድና የስርዓታዊ ብልሹነት ስለሆነ፣ ብሎም የዳቦንና የመብትን ጥያቄዎች ከአገራዊ ሕልውና ጥያቄ ጋር አያይዞ መታገል ወቅታዊ ብልህነት ስለሆነ፣ ኢሕማጉ አቋሙን እንደሚከተለው ለማስመር ይወዳል፡-

፩ኛ) በአገሪቱ ላይ ላለፉት ሶስት አስር አመታት የተዘረጋው ሰቆቃ በሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ላይ የተከሰተ በመሆኑ ቢያንስ የተናበበ የሕዝብ እምቢተኝነት አምባገነኖችን ከጫንቃችን ላይ በዘላቂነት ለማውረድ ቁልፍ ሚና እንዳለው እናምናለን።

፪ኛ) ይህ ግንዛቤ እንዳለ ሆኖ እያንዳንዳንዱ የሙያ ክፍል የተናጠል ጥያቄውን በሚመቸው መንገድ የማቅረብ መብትና ግዴታ እንዳለውም እንገነዘባለን፣ እንደግፋለንም።

፫ኛ) እንደ ጤና ባለሙያዎችና መምህራን ያሉ የበቃንና የይቻላል ንቅናቄዎች ሲጀመሩ አመራሮቹ የገኙሯውን ቡድን መሰረታዊ ባሕሪያት ተገዝቦ የሚተካካ አመራር በማዘጋጀትና የትግል ስልቶችን እንደ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች የመተለም አቅም መገንባት ያስፈልጋል። ትግሉም በዘላቂነት ፍሬያማ እንዲሆን መሪዎች ለመቀጣጫ ሲታሰሩ ብዙሃኑ ታጋይ የማያወላዳ ድጋፉን መግለጽ፤ አጋርን ማብዛትና የትግሉ ግቦች አገር-አቀፍ እንዲሆኑ መጣር በተራ በተራ ከመመታት ያድናል፤ የዳቦ ጥያቄ የነጻነት ጥያቄ መነሻ ሊሆንም ይገባዋል።

፬ኛ) ስለዚህ በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ያላችሁ ኢትዮጵያዊያን ትከሻ ለትከሻ ተደጋግፋችሁ እንደ ሰደድ እሳት እየተስፋፉ ያሉትን የሕዝብ እምቢተኝነት ንቅናቄዎች በጥሞናና ባስቸኳይ እንድትደግፉ አክብሮታዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ድል ለደፋር የጤና ባለሙያዎች!!

ድል ለታፈነው የኢትዮጵያ ሕዝብ!!